

# ኢትዮጵያ

## የአገር ውስጥ የመረጃ ሰነድ 2025

Funded by:

Federal Office for Migration and Refugees

RETURN

IOM UN MIGRATION

# አሳታሚው


**International Organization For Migration (IOM) Germany**

Charlottenstraße 68
10117 Berlin
Germany
T. +49 911 43 000
F. +49 911 43 00 260

iom-germany@iom.int
https://germany.iom.int/



ይህ ፕሮጀክት ከጀርመን ፌደራል የፍልሰት እና የስደተኞች ቢሮ ((BAMF) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የሚካሔድ ነው። (BAMF).



Tአይኦኤም የመረጃ ማሰባሰብ ስራውን በከፍተኛ ጥንቃቄ አከናውኗል። አይኦኤም ባለው እውቀት እና መረጃ ሁሉ መረጃዎችን ይሰጣል። ሆኖም ግን አይኦኤም በተሰጡት መረጃዎች ትክክለኝነት ላይ ተጠያቂ ሊሆን / ሃላፊነት ሊወስድ አይችልም ። በፍቃደኝነት ለመመለስ እና ለመቋቋም ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት የሚከተለውን ድህረገጽ ይጬኑ www.ReturningfromGermany.de, ወይንም በሀገርዎ የሚገኘውን በፍቃደኝነት የመመለስ እና የመቋቋም ቢሮ ያነጋግሩ።

የታተመ፡ ዲሴምበር 2025 - © IOM July 2025 Information may be outdated due to dynamic developments in the country.


# ማውጫ


1. የጤና ክብካቤ
2. የሰው ሀይል እና ቅጥር
3. ቤት
4. ማህበራዊ ዋስትና
5. የትምህርት ስርአት
6. ልጆች
7. የተጠሪዎች መረጃ እና ጠቃሚ አድራሻዎች/ማስፈንጠሪያ
8. በጨረፍታ
9. የድረ ገጽ ምክክር

### አጠቃላይ መረጃ

በኢትዮጵያ ውስጥ የጤና ክብካቤ አገልግሎት ለማግኘት የሚቻልባቸው አራት መንገዶች አሉ:: የመጀመሪያው የጤና ክብካቤ አገልግሎትን ከመንግስት ጤና ጣቢያዎች ወይም ሆስፒታሎች በአነስተኛ ክፍያ ወይም ከስደት ተመላሹ የሕክምና ወጪውን ለመሸፈን የሚያስችል በቂ አቅም የሌለው መሆኑን የሚያረጋግጥለት ማስረጃ የሚያቀርብ ከሆነ በነፃ ማግኘት ይችላል። ይህ ደብዳቤ የሚሰጠው ከሚኖርበት ቀበሌ ነው። ሁለተኛው አማራጭ ከስደት ተመላሹ ከግል ክሊኒኮች/ሆስፒታሎች በራሱ በሚሸፈን ከፍተኛ የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የሚያገኘው የጤና ክብካቤ አገልግሎት ነው። 3ኛው አማራጭ ከስደት ተመላሹ የጤና መድን ዋስትና አገልግሎት የሚሰጡ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ውስጥ መግባት የሚችልበት ነው:: የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሙሉ የጤና ክብካቤ ሽፋን የሚሰጥ
የመድን ዋስትና አገልግሎት ይሰጣሉ። ከፍተኛ ክፍያ የሚከፍለውን የህይወት መድን ዋስትና ፖሊሲ ለማግኘት የኢንሹራንስ ኩባንያው የግለሰቡን የጤና ሁኔታ አጣርቶ በዚሁ መሠረት የአረቦን ክፍያውን ይወስናል። የመጨረሻው አማራጭ የኢትዮጵያ መንግስት የጤና መድህን ስርዓት “ጤናመድህን” በመባል የሚታወቅ ሲሆን በሀገሪቱ ሁለት አይነት የጤና መድህን ስርዓቶች አሉ።የመጀመሪያው የጤና መድህን ስርዓት ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን (CBHI) ሲሆን ይህም መደበኛ ባልሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ የተሰማራውን ማህበረሰብ ያቀፈ ነው።ሁለተኛው የጤና መድህን ስርዓት ደግሞ ማህበራዊ ጤና መድህን (SHI) ሲሆን ይህም በመደበኛው የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩትን ግለሰቦች ያካትታል።በዚህ ስርአት ለመታቀፍ ግለሰቦች ወይም ቤተሰብ ቅድመ ክፍያ መዋጮ መክፈል አለበት። ይህም በሕመም ጊዜ እና ከአደጋ የጤና ወጪዎች ለመጠበቅ ያገለግላል, በሌላ አነጋገር, የጤና ኢንሹራንስ የፋይናንስ ችግርን በማስቀረት አነስተኛ መዋጮዎች በአንድ ላይ የሚሰበሰቡበት ቅድመ ክፍያ ሥርዓት ነው

### ጥቅማጥቅሞች:

የግል የመድን ዋስትና ኩባንዎች ሙሉ የጤና ክብካቤ ሽፋን የሚሰጡ የጤና መድን ዋስትናዎችን ያቀርባሉ:: እንደውስጥ ታካሚ አንድ ደንበኛ ሙሉ ሽፋን ማግኘት የሚችል ሲሆን ከዚህ በኋላም ከሆስፒታል ከወጣ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ጥቅማጥቅሞቹን ማግኘት ይችላል። በዚህ ውስጥም በውጭ አገር ህክምና ለማግኘት ሁኔታዎች በሚመቻቹበት እድል እንዲካተት ተደርጓል።

### ወጪዎች:

የኢትዮጵያ ጤና ዘርፍ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሲሆን እነዚህም ክትባት፣ የኤችአይቪ ኤድስ የምክር አገልግሎት እና የሳንባ ምርመራ እና ሕክምና እንዲሁም ቫይረሱ ቅድመ ወሊድ ክትትል እና የማዋለድ አገልግሎት ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል የሚሰጠውን ህክምና ከክፍያ ነፃ በማድረግ አገልግሎት ይሰጣል። ከዚህ በላይ ከተገለፁት አገልግሎቶች ውጪ ሌሎች አገልግሎቶች የሚሰጡት በክፍያ ነው።

### የጤና ሕክምና እና መድሃኒት

የሕክምና ተቋማት እና የህክምና ባለሙያዎችኢትዮጵያ ውስጥ የግልና የመንግስት ሆስፒታሎች አሉ በወረዳ ወይም ዞን ደረጃ ተቀዳሚው የክብካቤ ደረጃ ጤና ኬላዎችን፣ ጤና ጣቢዎችን እና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታልን ያካትታል። ሁለተኛው የክብካቤ ደረጃ አጠቃላይ ሆስፒታሎችን የሚያካትት ሲሆን በ3ኛ ደረጃ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ የግል እና የመንግስት ሆስፒታሎች ያሉ ሲሆን አብዛኛዎቹ የሚገኙት በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ውስጥ ነው። ስፔሻላይዝድ ሪፈራል የህክምና ተቋም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ ሲሆን ስልክ ቁጥሩ +251 1 111 1111

በኢትዮጵያ ያለው የዶክተር እና የታካሚ ጥምርታ በጣም ዝቅተኛ ነው፣ በቅርብ ጊዜ የተገመተው ግምት ለ5,843 ሰዎች አንድ ሐኪም ገደማ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መጠነኛ መሻሻል ቢታይም፣ ከ20,000 ሰዎች ከአንድ ሐኪም ወደ አሁኑ አኃዝ በመሸጋገሩ፣ አሁንም ለሀገሪቱ የጤና አጠባበቅ ሥርዓት ትልቅ ፈተና ነው።ወደ ሆስፒታል ገብቶ ለመታከም የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች:

አንድ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ተኝቶ ለመታከም ጉዳዩ በሀኪሞች ብቻ ታይቶ የሚፈቀድ

1 የጤና ክብካቤ

ሲሆን ከሕክምና ክፍያ ውጪ ሌላ መስፈርት የለም። ሕክምና ስለማግኘት እና የሕክምና ወጪ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ መድሃኒቶችን እና ዋጋዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ከዚህ በታች ያለውን ማስፈንጠሪያ ይጠቀሙ

http://haiweb.org/wp-content/uploads/2016/12/Price-Availability-Local-vs-imported-Meds-in-Ethiopia.pdf



Photo: IOM/ Olivia Headon 2019

**የጤና ክብካቤ ስርአት: ከስደት** ተመላሾች አገልግሎት ስለሚያገኙበት ሁኔታ

አገልግሎቱን ለመጠቀም ብቁ ስለመሆን እና መስፈርቶች:

ሁሉም አይነት ኢንሹራንስ ለሁሉም ክፍት ናቸው የስራ ምድቦቻቸው በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆኑት።

**የምዝገባ ስነ ስርአት**

በመንግስት ጤና መድን ለመመዝገብ ተመላሹ ለኢትዮጵያ ጤና መድን ኤጀንሲ ለእሱ ወይም በቤተሰብ ደረጃ ማመልከት እና በየወሩ አነስተኛ መዋጮ መክፈል ይኖርበታል።

መስፈርቶች

ቀበሌ መታወቂያ፣ የስራ መታወቂያ ወይም ብሔራዊ መታወቂያ

### አጠቃላይ መረጃ

በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው ህዝብ የሚተዳደረው የአገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት በሆነው በግብርና ዘርፍ ነው። በ2017 የቀረበው ሪፖርት እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አጠቃላይ አምራች የሚባለው የሰው ሀይል ብዛት 51.449.891 ሲሆን ይኽም የአለም ባንክ የልማት ጠቋሚዎች በሚል ከሰበሰበው መረጃ እና ይፋዊ እውቅና ከተሰጣቸው ምንጮች ተጠናቅሮ በቀረበ መረጃ መሠረት የተገኘ ነው። የስራ እድል ለህዝብ ብዛት ያለው ምጣኔ በገጠር አካባቢ 84.4 በመቶ ሲሆን ይህም በከተሞች አካባቢ ካለው 61.6 በመቶ አንፃር ከፍተኛ ነው። ይህም የሆነው በዋናነት በኢትዮጵያ ውስጥ የግብርና ዘርፍ ከፍተኛ የስራ እድል በመፍጠሩ ምክንያት ነው (የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒሲቴር 2015)። አነስተኛው የሰራተኛ እድሜ 14 አመት ሲሆን እድሜያቸው ከ14 እስከ 18 አመት የሆናቸው ህፃናትን ሕጉ በተለያየ መንገድ ጥበቃ የሚያደርግላቸው ሲሆን ከ7 ሰአት በላይ እንዳይሰሩ ገደብ ያደርጋል። በ2013 ለተሰራው የሰው ሀይል ጥናት መሠረት በከተማም ሆነ በገጠር አካባቢዎች ከፍተኛውን የስራአጥ ቁጥር የሚይዙት ሴቶች ሲሆኑ ከእድሜ አንፃር ስራ አጥነት በወጣቶች ላይ በስፋት ይታያል በከተሞች አካባቢ ያሉ ወጣቶች ለስራ አጥነት ችግር የተጋለጡ ናቸው። በ2013 የተሰራው የሰው ሀይል ጥናት ግኝት እንደሚያሳየው የስራ አጥ ወጣቶች መጣኔ ከአዋቂ ስራ አጥ አንፃር በ3 እጥፍ እንደሚበልጥ ያሳያል።

### የስራ ቅጥር የሚገኝባቸው መንገዶች/የሚደረግ ድጋፍ

የኢትዮጵያኖችን የስራ እድል አማራጮች በተመለከተ ከሚከተሉት መረጃ ያግኙ፡ የኢትዮጵያ የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (ሞልሳ) www.molsa.gov.et ከዚህ በታች የተቀመጠው ማስፈንጠሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያዎችን ወደሚያትም ድረገፅ ይወስዳል፡

- http://www.ethiojobs.net
- http://www.4icj.com/et
- http://www.employethiopia.com
- http://www.ezega.com
- https://www.ethiopianreporterjobs.com/
- https://reliefweb.int
- https://etcareers.com

### ለስራ አጥ የሚደረግ ድጋፍ

በኢትየጵያ ውስጥ ስራ ለሌላቸው ግለሰቦች ድጋፍ የሚያደርግ የስራ አጥ ሰዎች ድጋፍ ስርአት የለም። በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ የሚፈፀመው የስራ ቅጥር በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስርአጥ ወጣት የስራ እድል የሚፈጥር መንገድ ነው። ይህ የመንግስት ቅጥር አገልግሎት የስራ እና ክህሎት ሚኒስተር ስር በተለያዩ የክልል መ/ቤቶች ውስጥ ትስስር በመፍጠር የሚፈፀም ነው። www.mowl.gove.et በአገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች የአነስተኛ እና ጥቃቅን ድርጅቶች ልማት ኤጀንሲዎች ከቴክኒክ እና ሙያል ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት እና ከአነስተኛ እና ጥቃቅን የብድር ተቋማት ጋር በመቀናጀት ስራአጥ ወጣቶችን የማደራጀት፣ የማሰልጠን እና የተለያዩ የስራ ዘርፎች ላይ በተለይም በማደግ ላይ ባለው የግንባታ ዘርፍ እና በግንባታ መሳሪያዎች ምርት ማምረት ዘርፍ ላይ የማሰማራት ኃላፊነት አለባቸው።

### ተጨማሪ ትምህርት እና ስልጠናዎች

ለተጨማሪ ትምህርት እና ስልጠና እባክዎ ይህንን ድህረ ገጽ ይጎብኙ ፡

**ለስራ አጦች የሚደረግ ድጋፍ፡ ከስደት ተመላሾች ተጠቃሚነት**

ብቃት እና መስፈርት፡

ከስደት ተመላሹ በሚኖርበት ቀበሌ በስአጥነት መመዝገብ አለበት።

የምዝገባ ስርአት፡

ከቀበሌ ጽ/ቤት ጋር ግንኙነት ማድረግ ብቻ

አስፈላጊ ሰነዶች፡

ሕጋዊ መታወቂያ ወረቀት

ወይም ብሔራዊ መታወቂያ

2 የሰው ሀይል እና ቅጥር



Photo: Unsplash 2018/ Ibrahim Rifath

## አጠቃላይ መረጃ

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ቤት ለመግዛትም ሆነ ለመከራየት በጣም ውድ ነው። ተጋላጭ ለሆኑ ተመላሾች ብቻ አይኦኤም ኢትዮጵያ በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ የትራንዚት ማዕከሎች ጊዜያዊ ማረፊያ አገልግሎ ይሰጣል። እነዚህ ጊዜያዊ ማረፊያ ማዕከላት ከስደት ተመላሾች ወደ አገራቸው እና ወደ መዳረሻ ቤታቸው ለመመለስ ተገቢውን ዝግጅት ለማድረግ ያግዛቸዋል። ወደ እነዚህ ጊዜያዊ ማረፊያ ማዕከላት የሚደርሱ ስደተኞች በአይኦኤም ወይም ጊዜያዊ የመጠለያ አገልግሎት ድጋፍ በአጋዥ ድርጀጅቶች በኩል በሚሰጡት የመጠለያ ድጋፍ ሰራተኞች መመዝገብ፣ መረጃቸው በማህደር መያዝ እና በቂ መረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፡ ፡ ይሁን እንጂ ከእነዚህ የትራንዚት ማዕከላት ወይም መጠለያ ስደተኞች መሠረታዊ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን የሚቆዩበት ጊዜ ከአንድ ሳምንት ሊበልጥ አይችልም። ከዚህ ጊዜያዊ ማረፊያ አገልግሎት ውጪ የመኖሪያ የቤት ድጋፍ የሚያደርግ ሌላ ድርጅት የለም። አብዛኛውንም ጊዜ የቤት ወጪ ከአዲስ አበባ ዉጪ ባሉ ክልሎች በአንጻራዊነት ይቀንሳል። ቤት ለመከራየት ሁለት አማራጮች አሉ፤ አንደኛው አከራዩ በሚኖርበት በዚያው ግቢ ውስጥ አንድ ክፍል ቤት መከራየት ወይም ኮንዶሚኒየም ለኮንዶሚኒየም ቤቶች ዋጋው ለስቱዲዮ ከ10,000-.13,000 ብር፣ ለአንድ መኝታ ክፍል 13,000-18,000 ብር ለሁለት መኝታ ክፍል 25,000- 30,000 ብር ነው።

•https://jiji.com.et/addis-ababa/houses-apartments-for-rent

•https://realethio.com/

•http://www.expat.com/en/housing/africa/ethiopia/houses-for-rent.html

•http://www.ethiopianproperties. com/

## መኖሪያ ቤት የሚገኝባቸው መንገዶች/የሚደረግ ድጋፍ

አብዛኛዎቹ ሰዎች ደላላዎችን እና የሪል ስቴት ወኪሎችን ለመጠቀም ይመርጣሉ። አብዛኛዎቹ እነዚህ ደላላዎች እና የሪል ስቴት ወኪሎች በአንድ ቋሚ ቢሮ ውስጥ ሆነው አይሰሩም። በመደበኝነት እነሱን ማግኘት የሚቻለው በግል መኖሪያ ቤታቸው ወይም በሞባይል ስልክ ቁጥራቸው ነው። ደላላዎች ለሰጡት አገልግሎት የመጀሪያውን ክፍያ 25 በመቶ ያስከፍላሉ። በዚህ ስራ ላይ ከተሰማሩት ጥቂት አስፈላጊ ኩባንዎች መካከል አንዱን በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል።

ሄሎ ደላላ

ስልክ፡ 8104 (በአገር ውስጥ ብቻ)

+251963140626 (ሞባይል)

ሃቢታት ኒው ፍላወር ሆምስ

-ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሪል ስቴት አልሚ

## ቤት ለመስጠት የሚደረጉ ማህበራዊ ድጋፎች

የኢትዮጵያ መንግስት የቤቶች ልማት ፕሮጀክት በ2013 ጀምሯል። በዚህ ፕሮጀክት ስራ ሶስት የተለያዩ አቅዶች ያሉ ሲሆን እነዚህም 10/90፣20/80 እና 40/60 ናቸው። የ40/60 ፕሮግራም መካከለኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች ትክክለኛ ምርጫ ሲሆን ሌሎቹ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች ነው። ይህ ማለት ከአጠቃላይ የሪል ስቴት ዋጋው ግለሰቡ 40 በመቶ ሲቆጥብ የዋጋውን 60 በመቶ ብድር ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማግኘት ይችላል ማለት ነው። በተጨማሪም አንድ ግለሰብ ልዩ የቁጠባ ሂሳብ ከከፈተ ገንዘቡን ለሌላ አላማ አውጥቶ መጠቀም አይችልም። ስለዚህ ፕሮጀክት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን ከዚህ በታች ያለውን መስፈንጠሪያ ይጠቀሙ

- http://addisbiz.com/component/tags/tag/66-40-60-20-80-10-90-condominium-apartments-in-addis-ababa
- Hello Dellala Tel: 8104 (only in country) +251 963 140 626 (mobile) Habitat New Flower Homes PLC real-estate Developer

ለዚህ ፕሮግራም የሚያስፈልገው ምዝገባ በ2013 ያበቃ ሲሆን አዲስ ከስደት ተመላሾች ለዚህ ፕሮግራም ብቁ አይሆኑም።





Photo: Unsplash / Moti Abebe 2019

# 4 ማህበራዊ ዋስትና

## አጠቃላይ መረጃ

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት የተወሰነ ሲሆን በዋናነት ማእከል የሚያደርገው በህዝቡ የጤና ፍላጎት፣ በአካል ጉዳተኛ ሰዎች ፍላጎት፣ ቤት አልባ ህፃናት እና በማህበረሰብ ልማት ላይ ነው። የእነዚህ አገልግሎቶች አብዛኛዎቹ በመንግስት ስፖንሰር የሚደረጉ እና ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን በቅርቡ በግል የተደራጁ የማህበራዊ ዋስት አገልግሎቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል።

## የጡረታ ስርአት

ጡረታ ተፈፃሚ የሚሆነው ለመንግስት ሰራተኞች እና ለግል ድርጅት ሰራተኞች ነው። ከወርሃዊ ደመወዝ ላይ የተወሰነው መጠን እየተቀነሰ ሰራተኛው አገልግሎቱን እየሰጠ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ እንዲጠራቀም ተደርጎ ግለሰቡ ጡረታ ከወጣ በኋላ በጡረታ አበል መልክ ይከፈለዋል፡፡ የጡረታ ክፍያ መጠን በደመወዝ መጠን ላይ ይመሰረታል። የኢትዮጵያ የጡረታ እቅድ አራት የተለያዩ የጡረታ ክፍያዎችን የያዘ ነው። (ምንጭ፡ የመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አዋጅ 714/2011 እና የግል ድርጅት ሰራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2001)፡

1. በእድሜ ገደብ የሚሰጥ ጡረታ እና ዳረጎት
2. በጤና ምክንያት የሚሰጥ ጡረታ እና ዳረጎት
3. በህይወት ላሉ የጡረተኛ ወራሾች የሚሰጥ ጡረታ እና ዳረጎት
4. በስራ ምክንያት የሚከሰት የመቁሰል አደጋ እና ዳረጎት

ጥቅማጥቅሞች በቁጠባ ታሪክ የገንዘብ መጠን መሠረት አንድ ግለሰብ ጡረታ ከወጣ በኋላ ወርሃዊ ክፍያ/ደመወዝ ያገኛል።

**የማህበራዊ ዋስትና ስርአት፡ ከስደት ተመላሾች ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ**

**ብቁነት እና መስፈርቶች:**

በኢትዮጵያ ማህበራዊ ዋስትና ስር ድጋፍ ለማግኘት የሚታወቁ መስፈርቶች የሉም፡፡ ማንኛውም ግለሰብ ለቀበሌው/ለአካባቢው አስተዳደር ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል።
የምዝገባ ስርአት
ወደ ቀበሌ በመሄድ በግል ማመልከት
አስፈላጊ ሰነዶች
የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ለምዝገባው መሠረታዊ ሰነድ ነው። ወይም ብሔራዊ መታወቂያ

## ተጋላጭ ቡድኖች

በኢትዮጵያ አውድ ሲታይ ተጋላጭ ቡድኖች የሚባሉት አካል ጉዳተኛ (አእምሮአዊና አካላዊ) ሰዎች፣ ሴቶች፣ ነፍሰጡር ሴቶች፣ እማወራ ሴቶች እና የሚያጠቡ እናቶች፣ አረጋዊያን፣ ከኤችአይቪ ጋር የሚኖሩ ሰዎች፣ በህገወጥ የሰዎች መነገድ ወንጀል ተጠቂ የሆኑ ሰዎች፣ እድሜአቸው ከ18 አመት በታች ለሆኑ ህፃናት፣ አናሳ የብሔር እና የሃማኖት አባላት ናቸው።

መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ለተጋላጭ ስደተኞች ተመላሾች በተለይም የወሲብ ጥቃት ለደረሰባቸው እና በህገወጥ የሰዎች መነገድ ወንጀል ለተዳረጉ የጥቃት ሰለባዎች ድጋፍ የሚያደርጉ ድርጅቶች አሉ። የመጠለያ አቅርቦት፣ ማገገሚያ፣ ማህበረ-ስነልቦናዊ ድጋፍ እና መልሶ ማቋቋም በነዚህ ድርጅት ከሚሰጡት ድጋፎች መካከል የሚጠቀሱት ናቸው።

ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል አንዳንዶቹ AGAR በጎ አድራጎት ማህበር፣ ጂኤስኤ (የደጉ ሳምራዊ ማህበር)፣ ንጋት እና ሌሎችም ናቸው።





Photo: IOM/ Olivia Headon 2018

### አጠቃላይ መረጃ

የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኮሌጆች እና የቴክኒክ ተቋማት ለአገሪቱ ልማት የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን እና የሰለጠኑ የቴክኒክ ባለሙያዎችን ያፈራሉ። በሺዎች የሚቆጠሩ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለአገሪቱ ልማት የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል ለማፍራት መሠረት ይጥላሉ። እ.ኤ.አ. በጥቅምት 2023 የኢትዮጵያ የትምህርት ሚኒስትር ብርሃኑ ነጋ የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት ላይ በርካታ አስደንጋጭ መረጃዎችን ይፋ አድርገዋል። የ2022 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል (የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ) ፈተና ከሰጡ 3,106 ትምህርት ቤቶች 43% ያህሉ አንድም ተማሪ ያለፈ እንዳልነበረ ዘግቧል።እና ለሁለተኛ ተከታታይ አመት በሀገር አቀፍ የትምህርት መልቀቂያ ፈተና ከተሳተፉት ተማሪዎች ከ96% በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች 50% ያነሰ ውጤት ነው ያስመዘገቡት። ይህ ማለት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት ብቁ መሆን አልቻሉም። የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት የሚያስፈልገውን አስተዋፅኦ ማበርከት የሚችለውን ተገቢውን የሰው ሀይል የማፍራት አላማ አለው። በቅርቡ የተለያዩ አለም አቀፍ ት/ቤቶች እና የግል ትምህርት ቤቶች የመዋለ ሕፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ኢንተርናሽናል እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ጣልያን፣ ግሪክ፣ ስዊድሽ እና የህንድ ኮሚዩኒቲ ስኩሎች ይጠቀሳሉ። በትምህርት እና ምርምር ተቋማት፣ በኢትዮጵያ ስለሚገኙ የትምህርት መረጃዎች እና ኮርሶች ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ የሚከተለውን ድረገፅ ይጠቀሙ፡ www.Ethiopianeducation.com.

### ወጪ፣ ብድር እና ለትምህርት አገልግሎት የሚመደብ ገንዘብ

በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ 12 ክፍል ድረስ በመንግስት ት/ቤት ትምህርት የሚሰጠው በነፃ ነው። ይሁን እንጂ በግል ት/ቤቶች ጥራት ያለው ትምህርት በውድ ክፍያ ይሰጣል። በግል ት/ቤቶች ክፍያው በተርም ከ100 እስከ 250 የአሜሪካን ዶላር የአሜሪካን ዶላር ድረስ ሲሆን በአብዛኛዎቹ ት/ቤቶች ውስጥ አንድ አመት አራት ተርሞች አሉት፡ ፡ ዩኒቨርሲቲዎችን በተመለከተ የወጪ መጋራት ፕሮግራም ያለ ሲሆን ተማሪዎች ያለምንም ክፍያ ትምህርቱን ያገኛሉ። ነገር ግን ከተመረቁ በኋላ እና ተማሪዎች ወጪውን በየወሩ ተቀናሽ እያደረጉ ይከፍላሉ። የግል ዩኒቨርሲቲዎች ክፍያውን ተማሪዎች ራሳቸው ይከፍላሉ ለአንድ የትምህርት አመት የሚከፈለው ወደ 500 የአሜሪካን ዶላር ገደማ ነው።

### ለውጭ ዲፕሎማዎች የሚያስፈልግ ማረጋገጫ

ከስደት ተመላሹ በትውልድ አገሩ ትምህርቱን ለመቀጠል/ስራ ለመቀጠር የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

- ይማሩበት ከነበረው ተቋም የተሰጣቸው የምዝገባ ደብዳቤ
- ከነበሩበት አገር ውስጥ ባለው ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ ለተመዘገበባቸው ኮርሶች የወሰደውን ዝርዝር ኮርስ እና ውጤት ማስረጃ
- ከነበሩበትአገር የትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የዲግሪ ወይም የዲፕሎማ እውቅና እንዲሁም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ ማረጋገጫ
- ከነበሩበት አገር ውስጥ ባለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ለሁሉም ሰነዶች የተሰጠ ማረጋገጫ
- በኢትዮጵያ የትምህርት ሚኒስቴር የዲግሪ ወይም የዲፕሎማ ህጋዊ ማረጋገጫ
- የትምህርት ስርአት፡ ከስደት ተመላሾች የሚመዘገቡበት ስርአት እና ተጠቃሚነት

### የትምህርት ስርአት፡ ከስደት ተመላሾች የሚመዘገቡበት ስርአት እና ተጠቃሚነት

በኢትዮጵያ ውስጥ ከስደት ተመላሽ ለሆኑ ሰዎች የተለየ የምዝገባ ስርአት የለም። ይሁን እንጂ ከስደት ተመላሾች በነበሩበት አገር ውስጥ ትምህርት ጀምረው ከነበረ ፤ የነበሩበት አገር መንግስት እና እዛዉ አገር ውስጥ ባለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተረጋገጠ የትምህርት ቤት ማስረጃ ማቅረብ

5 የትምህርት ስርአት



Photo: Unsplash/ Gift Habeshaw 2019

## የልጆች እና ሕፃናት አጠቃላይ ሁኔታ

ኢትዮጵያ የወጣት መገለጫ ናት። ከሕዝቧ ግማሽ በጥቂት ያነሰ፤ ወይም ወደ 49.5 ሚሊዮን የሚሆኑ ሕፃናት ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች ናቸው፡ ፡ ከእነዚህም ውስጥ 15.2 ሚሊዮን የሚሆኑት ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ናቸው፡ ፡ በጣም የቅርብ ጊዜው የብሔረሰብ፣ የቋንቋ እና የእምነት ቡድኖች የስነሕዝብ መረጃ የወጣው በእድሜ ወይም በጾታ ካልተለየው የ 2007 የህዝብ ቆጠራ ነው። በዚህ ቆጠራ የልጆች ቁጥር አይታወቅም። ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የህጻናትን መብቶች ስምምነት እ.ኤ.አ. በ 1991 አፀደቀች። የእሱ አማራጭ ፕሮቶኮሎች እ.ኤ.አ. በ 2014 እና በ የአፍሪካ የህፃናትን መብትና ደህንነት ቻርተር እ.ኤ.አ. በ 2002 ፈርማለች። እ.ኤ.አ. በ 1994 የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት የህፃናትን መብትና ደህንነት ለመጠበቅ አንድ አንቀፅ ይዟል። የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስተር በአገር አቀፍ ደረጃ የሕፃናትን መብቶች እና የሕፃናት ጥበቃን ያስተባብራል። ኢትዮጵያ የእናቶችን እና ከአምስት አመት በታች ህፃናትን ሞት በመቀነስ ኤች.አይ.ቪን፤ ወባ እና ሌሎች በሽታዎች፤ በመዋጋት ረገድ ከፍተኛ እድገት ብታሳይም አሁንም ግን ተግዳሮቶች አሉ። በአጠቃላይ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ልጆች በብዙ አቅጣጫ የተቸገሩ ናቸው ፤ ከመሰረታዊ ሸቀጦች እና አገልግሎቶች ቢያንስ በሦስት ልኬቶች ተነፍገዋል ማለት ነው ይላል በማእከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጄንሲ እና በዩኒሴፍ የወጣው አዲስ ዘገባ። መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከ 2000 ጀምሮ የእናቶች እና የህፃናት ሞት እያሽቆለቆለ መጥቷል። ይሁን እንጂ አዲስ የተወለዱ ሞት እጅግ ከፍ ያለ ነው። ጥራት ያለው የቅድመ ወሊድ ፤ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ ጤና አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆን፤ በተለይም በገጠር አካባቢዎች፤ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ያደናቅፋል። በመጀመሪያዎቹ 28 ቀናት ውስጥ አዲስ የተወለዱትን ሞት መቀነስ አሁንም ፈተና ነው። በቀላሉ ሊከላከሉ በሚችሉ በሽታዎች 480 ሕፃናት በየቀኑ ይሞታሉ።

በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች በሴት ብልት መገረዝ (መቁረጥ) (ግርዛት) እና ያለእድሜ ጋብቻ በጣም የተጎዱ ናቸው። የሴት ልጅ ግርዛትን በመፈፀም አገሪቱ በዓለም በሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፣ ይህውም የሴቶች ቁጥር (ከ15-49 ዓመት ዕድሜ ያላቸው) 23.8 ሚሊዮን ነው።

የሴቶችና ሕፃናት ሚኒስቴር የሕፃናትን መብቶች እና የሕፃናት ጥበቃን በአገር አቀፍ ደረጃ ያስተባብራል፣ ሆኖም የልጆችን ደህንነት እና መብቶች በሚመለከት የሚሰሩ ዓለም አቀፍ፤ የሃገር ውስጥ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት አሉ። ሁሉም ድርጅቶች ማለት ይቻላል ለህፃናት መርሃግብሮች አሏቸው ነገር ግን አንዳንድ ድርጅቶች በልጆች ላይ ብቻ የተካኑ ናቸው፣ ለምሳሌ ዩኒሴፍ፣ ሴቭ ዘ ችልድረን፣ ኦፒአርስስ።

### መንግስታዊ የሆኑ/ያልሆኑ የህፃናትን ደህንነት እና መብቶች ዙሪያ የሚሰሩ አካላት

- ዩኒሴፍ በተሻሻለ የህፃናት ህልውና፣ ልማትና ጥበቃ የህፃናትና የሴቶች መብትን እውን ለማድረግ ብሄራዊ ጥረቶችን ለመደገፍ ይሠራል።
- ሴቭ ዘ ችልድረን ኢትዮጵያ የልማት እና ሰብዓዊ ሥራዎችን በእኩልነት የመደገፍ የሕፃናት አድን የሕፃናት ሁለት ኃላፊነት እውን እንዲሆን ቁርጠኛ ሆና ትቀጥላለች። በኢትዮጵያ በሰባት ዋና ዋና የፕሮግራም ዘርፎች ውስጥ የምንሰራው ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን እና ቤተሰቦቻቸውን በማነጣጠር በአብዛኛው በገጠር እና በሩቅ እና ዝቅተኛ አገልግሎት ባልተሰጣቸው አካባቢዎች ነው።
- ኦፕሪፕስ (ሴት የጎዳና ልጆችን ወደጎዳና ከመውጣት መከላከል፣ መልሶ ማ¬ቋቋሚያ እና ውህደት ድርጅት)
- የወጣት ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ደህንነቱ የተጠበቀ ፍልሰት ማስፋፋት ላይ ያተኩራል፡ ፡ ሴት የጎዳና ልጆችን ወደጎዳና ከመውጣት መከላከል፣ መልሶ ማቋቋሚያ እና ውህደት ድርጅት በራስ አገዝ ቡድኖች አማካይነት በጣም ድሃ የሆኑ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ኢኮኖሚያዊ ኑሮ ለማሻሻል ይፈልጋል። የተሻሻሉ የሥራ ሁኔታዎችን ከቀጣሪዎች ጋር ለመደራደር በተለይ በአሁኑ ወቅት በቤት ውስጥ ሥራ ላይ ተሰማርተው ከሚሰደዱት ጋር ይሰራል። እንዲሁም ተመላሾችን እና ስደተኞችን

6 ልጆች

- ሊሆኑ የሚችሉ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ማንነት ለማሻሻል ኦፕሪፕስ ለተመላሾች የልዩ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የማህበረሰብ ውይይቶችን ያደራጃል እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ትብብር ያጠናክራል።

ቻይልድ ፈንድ ኢትዮጵያ በልጆችና እናቶች ጤና አገልግሎቶች፣ የሕፃናት ከለላ፣ የተመጣጠነ ምግብ፤ የቅድመ መደበኛ ህጻናት እድገት አገልግሎቶች ተደራሽነት፣ ወላጅ ያጡ ልጆች ድጋፍ፣ የኢኮኖሚ ማጠናከሪያ፣ የውሃ እና የአካባቢ ጽዳትና የግል ንፅህና እንዲሁም በወላጅ እና በአሳዳጊ ትምህርት ላይ ያተኩራል።

ቻይልድ ፈንድ ኢትዮጵያ በልጆችና እናቶች ጤና አገልግሎቶች፣ የሕፃናት ከለላ፣ የተመጣጠነ ምግብ፤ የቅድመ መደበኛ ህጻናት እድገት አገልግሎቶች ተደራሽነት፣ ወላጅ ያጡ ልጆች ድጋፍ፣ የኢኮኖሚ ማጠናከሪያ፣ የውሃ እና የአካባቢ ጽዳትና የግል ንፅህና እንዲሁም በወላጅ እና በአሳዳጊ ትምህርት ላይ ያተኩራል።



# 7 የተጠሪዎች መረጃ እና ጠቃሚ አድራሻዎች

Association for Women's Sanctuary and Development (AWSAD)
Addis Ababa, Bole sub city Woreda 4,H. No140
Tel.: +251116672290
Email: www.awsad950@gmail.com

Good Samaritan Association
Addis Ababa, Gulele subcity 01 woreda,Shiromeda
Tel.: +251 111 242 952
Email:goodsamaritan1996@gmail.com
Internet: https://gsaethiopia.org

Agar Ethiopian Charitable Society
*Charity*
Addis Ababa, Kirkos sub city, House no.383
Tel.: +251 930098695
Email: info@agarethiopia.com
Internet: www. agarethiopis.org

---

Association for Forced Migrants (AFM)
*Forced migration*
Addis Ababa, Nefassilk Lafto Sub City, Woreda 3
Tel.: +251-113718712
Email: aardr@ethionet.et
Internet: www.afmethiopia.org

African Network for Prevention and Protection of Children Against Maltreatment and Neglect (ANPPCAN)
*Child protection*
Addis Ababa, Kirkos Sub City Woreda 18, H.No. 743-Tel.: +251 911 640 739-Email: annp-can-eth@ethionet.et-Internet: www.anppcanethiopia.org

International Committee of the Red Cross (ICRC)
*NGO*
Bole Sub-City, K. 12/13 H. No. New, Addis Ababa
Tel: +251-11 647 83 00
Email: addis_abeba.add@icrc.org
Internet: www.icrc.org

---

Organization for Prevention, Rehabilitation and Integration of Female Street Children (OPRIFS)
*Children*
Addis Ababa
Tel.: +25191112365410
Email: info@oprifs.org.et

UNICEF
*Children*
Opposite German House, Addis Ababa Ethiopia
Tel.: +25115184013
Email: ethcommunication@unicef.org
Internet: www.unicef.org

Union of Ethiopian Women Charitable Associations (UEWCA)
*Children*
Addis Ababa, Ethiopia
Tel.: +251 911 407 136
Email: uewca@yahoo.com
Internet: www.uewca.org.et

---

Ethiopian Ministry of Health
*Health*
Sudan Road (Ministry of Health), 6th floor
P.O. Box 1234,Addis Ababa
Tel: +251 115 517 011

Bureau of Labour and Skill
*Labour administration*
Behind Lambert Ethiopian Technical and Vocational Institute
Tel.: +251 116 671792
Email: info@Mols.gov.et

Ethiopian Insurance Corporation
*Insurance*
Addis Ababa
Tel: +251 11 551 24 00
Email: eic.mdxvs@ethionet.et
Internet: http://www.eic.com.et

---

Benishangui- Gumuz Micro Finance
*Microfinance*
Assosa
Tel.: +251 57-775 0 666
E-mail: bgmf@ethionet.et

Adeday Micro finance
*Microfinance*
Mekelle
Tel.: +251 914 543 004

Save the Children
*Children*
Tel: +251 11 372 8455-65
Fax: +251 11 372 8045
ethiopia.savethechildren@savethechildren.org

# 8 በጨረፍታ

### ከመመለሱ በፊት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

- ሰነዶች-እሱ/እሷ ትክክለኛ የጉዞ ሰነድ መያዙን ያረጋግጡ፡፡ ተመላሹ ትክክለኛ ፓስፖርት ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ ከሌለው፤ የይለፍ ወረቀት ለማግኘት በጀርመን የኢትዮጵያ ኤምባሲን ማነጋገር አለበት፡፡ ተመላሾቹ እንደ መንጃ ፈቃድ ፤ የትምህርት ቤት የምስክር ወረቀቶች፤ ዲፕሎማ እና ዲግሪ፤ የልደት የምስክር ወረቀቶች ያሉ ሰነዶች ካሏቸው፤ ባሉበት ሀገር ውስጥ ባለው ኢትዮጵያ ኤምባሲ ማረጋገጥ አለበት፡፡ ከመመለሳቸው በፊት ያሉበት ሀገር የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ያሳውቁ፡፡
- መጠለያ- ተመላሹ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ መጠለያን በተመለከተ ሁሉም አስፈላጊ ዝግጅቶች መደረጋቸውን ያረጋግጡ፡፡
- መጓጓዣ- የጉዞ ዝርዝሮችን እና ወደ መጨረሻው መድረሻ መጓጓዣን በተመለከተ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን ያግኙ፡፡
- ጤና- ክትባቶችን ይፈትሹ፡፡ ኢትዮጵያ ለመግባት የቢጫ ወባ ክትባት መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ የሕክምና ታሪክ ይዘው ይምጡ፡፡
- በሁለት የኢትዮጵያ ክልሎች ማለትም በአማራ እና በትግራይ ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት ዜጎችን በፈቃደኝነት ላይ የታገዘ የመመለስ ስራ ሙሉ በሙሉ ተቋርጧል። በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በፍቃደኝነት ወደ ሌሎች ክልሎች ለመመለስ የሚፈልጉትን ፍልሰተኞች ማገዝ እንደሚቻል ዋና መ/ቤቱ ፈቅዷል። በሌላ አነጋገር አይኦኤም ኢትዮጵያ ወደነዚህ በሁለት ክልሎች ለመመለስ እቅድ ላላቸው ፍልሰተኞች ምንም አይነት ድጋፍ አያደርግም።
- አገልግሎቱ በማንኛውም የፋይናንስ ተቋም፣ ባንኮች፣ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ቢሮዎች እና የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጽ/ቤቶች ይገኛል።

### ከተመለሱ በኋላ ወዲያው መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

- መግቢያ- በሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ ፓስፖርቱ በኢሚግሬሽን ማህተም ይደረግበታል፡፡የሁለተኛ ክፍያቸው መሰብሰብ/የሃገር ውስጥ መታወቂያ እስኪያገኙ ድረስ የፓስፖርቱ ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ አገልግሎት ቢያንስ ስድስት ወር መሆን አለበት፡፡
- መታወቂያ-ከተመለሰ በኋላ ማድረግ ያለብዎት ዋናው ነገር ለብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ማመልከት ነው፡ ፡ በአገሪቱ ውስጥ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ለማስኬ ድብሔራዊ/የመኖሪያ መታወቂያ ካርድ ግዴታ ነው፡፡ማንኛውም ተመላሽ በሀገር ውስጥ ለስድስት ወራት መቆየት ሳያስፈልገው ለብሔራዊ መታወቂያ ማመልከት ይችላል። ይህ ማለት የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ተነስተዋል ማለት ነው። አገልግሎቱ በማንኛውም የፋይናንስ ተቋም፣ ባንኮች፣ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ቢሮዎች እና የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጽ/ቤቶች ይገኛል።
- ስልክ-ተመላሹ ከተመለሰ በኋላ ወዲያውኑ የአካባቢውን ቴሌኮሙኒኬሽን በአካል በማመልከት የስልክ ቁጥር ማግኘት ይችላል፡ ፡
- መልሶ ማቋቋም-ተመላሾቹ መመለሳቸውን ተከትሎ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከአይኦኤም ቢሮ ጋር በመገናኘት ስለ መልሶ ማቋቋሚያ እቅዳቸው መወያየት አለባቸው፡፡ጥቃቅን ንግድን ለመጀመር ለሚፈልጉ ሁሉ የገቢያውን እና ተግባራዊ የንግድ ዕድሎችን መገምገም አስፈላጊ ይሆናል፡
- ማህበራዊ ውህደት-ተመላሾች ማህበራዊ ውህደታቸውን በሚያፋጥኑ የተለያዩ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች (እድር፣እቁብ) ለመሳተፍ መሞከር አለባቸው፡፡

# 9 የድረ ገጽ ምክክር




### ፍልሰተኞች እርዳታ በኢትዮጵያ

የቨርቹዋል የምክር አገልግሎት ፕሮጀክት በጀርመን በአለም አቀፍ የፍልሰተኞች ድርጅት (አይኦኤም) ይተገበራል፡፡በጀርመን ውስጥ የሚኖሩ እና ለመመለስ የሚያስቡ ስደተኞች በኢትዮጵያ ውስጥ በአይአይኤም ሰራተኞች የመመለስ እና መልሶ የማቋቋም ምክር ይሰጣቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ያሉ የአይኦኤም ሰራተኞች በበይነ መረብ አማካኝነት በእንግሊዝኛ እና በአማርኛ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡

ይህ አገልግሎት ስደተኞችን ስለመመለሻ እና መልሶ የማቋቋም አማራጮችን እና የእርዳታ ፕሮግራሞችን በማሳወቅ ክብራቸው እንደተጠበቀ እንዲመለሱ ለማስቻል ያለመ ነው፡፡

**አድራሻ፡ ቤተልሄም/አይኦኤም ኢትዮጵያ**

ዋትስአፕ +251 944 335 395
ሐሙስ ከ12:30 እስከ 3:30 ከሰአት (CET)
የአውሮፓ መካከለኛ ሰአት